# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከአፍሪካ ቀዳሚ ይሆናል

ኢትዮጵያ እ.አ.አ በ2010 – 2011 አጠቃላይ አገራዊ የምርት መጠኗ ከአጠቃላይ የአፍሪካ አገራት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ እድገትና ብልጫ እንደሚያሳይ የአፍሪካ ልማት ባንክ አስታወቀ።

ባንኩ ያዘጋጀው የአፍሪካን የ2010 ኢኮኖሚያዊ ገጽታ በሚያሳይ ሪፖርቱ ላይ ኢትዮጵያ በ2015 የምእታመቱን የልማት ግቦች ያሳካሉ ተብለው በግንባር ቀደምትነት ከተጠቀሱ ሶስት አገሮች አንዱ መሆኗንም ጠቅሷል።

በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በቀረበው በዚሁ ሪፖርት 50 የአፍሪካ አገራት ተካተዋል።

በሪፖርቱ እንደቀረበው እ.ኤ.አ በ2009 ከአፍሪካ አገሮች አጠቃላይ አገራዊ የምርት መጠን ኢትዮጵያ 9.9 ኮንጎና 7.6 ማላዊ 7.0 እድገት በማስመዝገብ በቅደም ተከተል ተቀምጠዋል።

በ2010 – 2011 ከአፍሪካ አገራት አጠቃላይ አገራዊ የምርት መጠን እድገት አሁንም ኢትዮጵያን 10.9 ከፊት ያስቀመጠው ሪፖርቱ በማስከተል አንጎላና 7.9 ኡጋንዳን 7.9 በመቶ የሆነ እድገት እንደሚያስመዘግቡ ሪፖርቱ ሙያዊ ግምቱን ገልጿል።

እንዲሁም የምእተ አመቱ የልማት ግቦች ያሳካሉ ካላቸው አገራት መካከል በግንባር ቀደምነት ኢትዮጵያ ሊቢያና ቱኒዚያ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ሪፖርቱ አስረድቷል።

ሪፖርቱ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ2003/2004 ጀምሮ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት ስታስመዘግብ ቆይታለች ካለ በኋላ በተለይ ባለፈው አስር አመት ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለግብርናና ለመንገድ ልማት በሰጠችው ልዩ ትኩረት አገሪቱ አስደናቂ ውጤት አስመዝግባለች ብሏል።

ሪፖርቱ በአፍሪካ ኢኮኖሚ ላይ ሰፊ ተቀባይነት ያለው አመታዊ ሪፖርት ነው ያሉት በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የኢኮኖሚ ልማትና የኔፓድ ክፍል ዳይሬክተር  ሚስተር ኢማኑኤል ናዶዚ ሪፖርቱ  በአጠቃላይ  በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ያለውን ማህበራዊና አስተዳደራዊ እድገት የሚዳስስ መሆኑን ጠቁመዋል።